# አመጽ ነው መፍትሄው

የሰማዩ ሳያንስ ፣ በምድርም ኩነኔ
መረገጥ መገፋት ፣ ዛሬም በወያኔ
ቃታውን ለመሳብ ፣ አጣንና ወኔ
ወልዶ ብቻ መቅበር ፣ ማለት ፣ ወይኔ ፣ ወይኔ!
እንደቅጠል መርገፍ ፣ በችጋር በጠኔ ።

ቀን ይወጣል ብሎ ፣ ሁሌም እየመሸ
ባላገር ተነጥቆ ፣ በጠኔ እየታሸ
ወያኔ በቁንጣን ፣ ጠግቦ እያቀረሸ
የሕዝብ ሀብት ዘርፎ ፣ ካገር እያሸሸ
ሚሊዮን ይሞታል ፣ ሆድ ሆዱን እያሸ ።

ንብረቱ ተሸጦ ፣ እሱም ተቀጥቅጦ
የሚያውቃት አገሩ ፣ መልኳ ተለውጦ
እፍኝ በማይሞሉ ፣ ባንዳዎች ተረግጦ
በገዛ ንብረቱ ፣ ድርቡሽ ፣ አረብ ፣ አብጦ
ባዕድ ጠግቦ ሲያድር ፣ ይብላ ወይ ፣ ቀላውጦ?
እንደምን ተሳነው ፣ መነሳት አምጦ?
ባመጽ መያዝ ሲቻል ፣ ስልጣኑን ገልብጦ ።

አገርህን ሸጠው ፣ አገር እያሳጡህ
ካደከበት ቀዬ ፣ ነቅለው እያወጡህ
በስምህ ለምነው ፣ ፍርፋሪ አይሰጡህ
ጦም ውለህ ፣ ጦም ባደርክ ፣ መልሰው ሲረግጡህ
በገንዘብ ፣ በስራት ፣ በሞት ፣ እየቀጡህ
ሞትና ድህነት ፣ ከቤትህ ላይወጣ
ምን ቀረኝ ብለህ ነው ፣ ላመጽ የማትወጣ?
በደሉን ለመድክ ወይ ፣ ምነው አትቆጣ?
ምን ትጠብቃለህ ፣ ምንስ እስኪመጣ?

ዘላለም ከማዘን ፣ ዘላለም ከማልቀስ
የምትናፍቀው ቀን ፣ በልመና ላይደርስ
የጎጠኞች ስርአት ፣ ተመንግሎ እንዲፈርስ
ተላብሰህ ተነሳ ፣ ያባቶችን መንፈስ
ዳር እስከዳር አገር ፣ ይረበሽ ፣ ይታመስ!
ወያኔ ይመተር ፣ አጥንቱም ፣ ይከስከስ
ደመ ከልብ ፣ ደሙ ፣ እንደ ጅረት ፣ ይፍሰስ
ሺ ፣ ወያኔ ይሙት ፣ አገርህ ሳትፈርስ
አንተም ፣ እንደ እንስሳ ፣ ተንቀህ ሳትረክስ
ይንቀልቀል እሳቱ ፣ የልባችን ይድረስ ።

ምን ታመነታለህ ፣ የምን ፈራ ተባ
በቁምህ አትሙት ፣ ዱር ጫካ እማትገባ?
ቢሻህ ፣ በከተማ ፣ መሀል አዲሳባ

አራውጠው ወያኔን ፣ እናቱ ሆድ እንደሁ ፣ ተመልሶ አይገባ
በሰፈራት ቁና ፣ ያልቅስ ፣ የደም እንባ
ደደቢት አይመሽግ ፣ያለው ካንተው አምባ ።

የባዕድ ቅጥረኛ ፣ የሚወድ ማውደልደል
ሀዘን የማይገባው ፣ አገርና ወገን ፣ ሲጠቃ ሲበደል
አንተም አትራራለት ፣ ጭራሽ ፣ ያንተም አይደል
አመጽ ነው መፍትሄው ፣ መሞትና መግደል
አመጽ ነው መፍትሄው ፣ መሞትና መግደል ።

ታዛቢው

November 11, 2009